# ሁለቱን ግንቦት 7ኦች የምንዘከረው የገባነውን ቃል በማደስ ነው!!!

## ከግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት 7 2002

ግንቦት 7 ለእኛ ልዩ ቀን ናት። ከሁሉ አስቀድሞ የዛሬዋ ግንቦት 7 የ1997 አምቷን የግንቦት 7 ቀን መታሰቢያ ናት። ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ለዲሞክራሲ የበቃን መሆናችንን ያስመሰከርንባት ዕለት ናት። ይህች ቀን ድምፃችንን የሚያስከብርልን ተቋም ቢኖረን ኖሮ እኛም እንደሰለጠኑት አገሮች ዜጎች የምርጫ ካርዶቻችንን ተጠቅመን የማንፈልጋቸው መሪዎች መሻር፤ የምንፈልጋቸውን ደግሞ መሾም የምንችል መሆኑን ለራሳችንም፣ ለመላው ዓለምም ያረጋገጥንባት ዕለት ናት። በዚች ታሪካዊ ዕለት የዲሞክራሲን ጣዕም በትንሹም ቢሆን ቀምሰናል።

ግንቦት 7 1997 ኢትዮጵያዊ አንድነታችን ከዘር፣ ከቋንቋ፣ ከሃይማኖት፣ ከፆታ፣ ከሃብትና ከእውቀት ልዩነቶቻችን በላይ የናኘባት ዕለት ናት። በታሪካችን ውስጥ የተወዳዳሪ ፓርቲዎችን ራዕዮች እና ፕሮግራሞች በየራሳችን የግል ሚዛን አስቀምጠን የመረጥንበት ብቸኛ አጋጣሚ ግንቦት 7 1997 ናት። ያችን የመሰለች ቀን በሺሆች ዓመታት ታሪካችን ውስጥ ኖሮን አያውቅም። ይሁን እንጂ የግንቦት 7 1997ቱ ፍስሃ አንድ ቀን እንኳን አብሮን ውሎ አብሮን አላደረም። በወያኔ አረመኔነት ደስታችን በምሬት፣ ተስፋችን በጽልመት ተቀየረ። ህፃናት በአደባባይ ተረሸኑ፤ ወጣቶች ተጋዙ፣ ተደበደቡ፣ ሰቆቃዎች ተፈጸሙባቸው፤ ወላጆች ስለልጆቻቸውና ስለራሳቸው አለቀሱ።

ግንቦት 7 1998 እና ግንቦት 7 1999ን ያሳለፍነው ሃዘንና ቁጭት ባጠላባቸው ድባቦች ውስጥ ሆነን ነበር። ሁለቱንም ዓመታት በ97 የተነጠቅነውን ነፃነትና ደስታ እና ያጣናቸውን ወገኖቻችንን በማስታወስ በሃዘንና በቁጭት አሳለፍናቸው።

ግንቦት 7 2000 ዓ. ም. ግን ሌላ ታሪካዊ ክስተት ተፈጠረ። ለግንቦት 7 1997 ዳግም ትንሳዔ የሚታገል፤ የ97 ቱን ጭላጭን ያዳፈኑብን እርጉሞችን በሁለገብ ትግል ለማንበርከክ የቆረጠ፤ በ97 ካጣነው በላይ መፍጠር እንችላለን ብሎ ያመነ ድርጅት ተወለደ። ራሱንም "ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ" ብሎ ሰይሞ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተሸጋገረ።

እነሆ ከዚያ ወዲህ ግንቦት 7ን በድርብ በዓልነት እናከብራለን። በአንድ በኩል ግንቦት 7 1997ን እንዘክራለን። በሌላ በኩል ደግሞ ግንቦት 7 2000 ዓ. ም. የተወለደውን ድርጅታችንን ተግባራት እንገመግማለን።

የግንቦት 7 1997ቱ የሕዝብ ዝግጁነት አሁንም አብሮን እንዳለ ጥርጥር የለንም። በተለያዩ አጋጣሚዎች ይህን ተመልክተናል። ግንቦት 7 2000 ዓ.ም የተፈጠረውስ ድርጅታችን ባሳለፍነው አንድ ዓመት ውስጥ ምን ከውኗል?

የግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመረጠው የትግል ስልት የተግባር ክንውኖች ለግልጽ ሪፖርት የሚመቹ እንዳልሆነ አባሎቻችን፣ ደጋፊዎቻችንና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይረዱልናል ብለን እናምናለን። ይሁን እንጂ እጅግ አጠቃላይ በሆነ መንገድ የሚከተሉትን ማለት እንችላለን።

1. ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ ድርጅታችን በአባላት ጥራትም ብዛትም ተጠናክሯል። የድርጅታችን መዋቅር በኢትዮጵያም ከኢትዮጵያም ውጪ ሥር ሰዷል። በራሱ በወያኔ ውስጥ ሳይቀር ማደራጀት ችለናል።

2. መላ አባላት ተሳትፎ ማድርግ በሚችሉባቸው የተለያዩ ዘርፎች ብንቃት የሚንቀሳቀሱባቸው የስራ መስኮች ዘርግተናልል።

3. የወያኔን ዘረኝነት በማስረጃዎች በማጋለጥ በዲፕሎማሲው ዘርፍ የማይናቁ ድሎችን ተቀዳጅተናል። ዛሬ ሁሉም መንግሥታት፣ የዜናና የምርምር ተቋማት ስለወያኔ ሠራዊት፣ ስለ ውጭ ጉዳይ መ/ቤቱ እና ሌሎች ቁልፍ ተቋማቱ ዘረኛ አወቃቀር በቂ ግንዛቤ አግኝተዋል።

4. አባሎቻችን በሲቢክ ማኅበራትና በሲቪክ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ ወያኔን ለማስወገድ የሚደረገው ሁለገብ ትግል በሁሉም ግንባሮች እንዲፋፋም ተደርጓል።

5. ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ ለመሥራት የማያቋርጥ ጥረት እየተደረገ ነው። በዚህም ረገድ አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል።

6. የወያኔን የሚዲያ አፈናን ለመበጠስ በሳምንት ሶስት ቀናት ጠዋትና ማታ በሚተላለፍ ሬድዮና በየሳምንቱ ከሚታተም የድርጅታችን ልሳን በተጨማሪ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። የወያኔን የሚዲያ አፈናን መስበር የምንችልበትን አቅም ገንብተናል።

7. ራሳችንን ከጥቃት ለመከላከል የምናደርገው ዝግጅት በሁሉም ረገድ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ከላይ የተዘረዘሩት ነገሮች መከወናቸው እውነት ቢሆንም በቂ ናቸው ብለን አናምንም። እንዲያውም ሃገራችንና ህዝቧ ከተደቀኑባቸው ከባድ ፈተናዎች ጋር ሲወዳደር የተሰራው ኢምንት ነው ማለት ይቻላል። መራራው የነጻነት ትግል የሚጠይቃቸውን የመስዋእትነት፣ የእውቀት፣ የቁሳቁስና የሌሎችም ግብአቶች መጠን በሚገባ የተረዳ ሃገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ሃይል በማህበረሰባችን ውስጥ ገንብተናል ማለት አያስደፍርም። ለዚህም ነው የዛሬው እለት መጪውን የስራ ሸክማችንን የምናስታውስበት እንጂ በተሰራው የምንኩራራበት ሊሆን አይገባውም የምንለው;; ይህ ስራ ደግሞ ዘረኛው ወያኔ ተወግዶ በሕዝብ ፈቃድ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን እስካልተረከበ ድረስ ሳንታክት ሳናርፍ ልናከናውነው የሚገባ ስራ ነው።

ስለሆነም የዛሬው ግንቦት 7 ትግሉ የሚጠይቀውን መራራ መስዋእትነት የምንዘክርበትና ወያኔን በሁለገብ ትግል ገጥመን ለመርታት ለራሳችን የገባነውን ቃል የምናድስበት ዕለት ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**